AEPAC

American Ethiopian Public Affairs Committee

February 8, 2023

# የአሜሪካን ኢትዮጵያዉያን ሕዝብ ጉዳይ ኮሚቴ (ኤፓክ) መግለጫ

ኤፓክ ከዓለም አብያተ ክርስቲያናት ካዉንስል (World Council of Churches)፤ የምስራቅና ኦሪየንታል ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት (Eastern and Oriental Orthodox Churches)፤ የኢትዮጵያ ሀይማኖቶች ካዉንስል (Inter-Religious Council of Ethiopia)፤ የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ካዉንስል (Ethiopian Human Rights Council) እና፤ ከበርካታ ታዋቂ የኢትዮጵያ ዳያስፖራ ማህበራትና ድርጅቶች፤ እንዲሁም ግለሰቦች ጋር በመሆን፤ በኢትዮጵያዉያን ላይ እየተፈጸመ ያለዉን ግፍና ሰብአዊ መብት ጥሰት በቶሎ እንዲያስቆሙና፤ ሀገራችን ኢትዮጵያን ከቁልቁለት ጉዞ እንዲመልሱ ለጠቅላይ ሚንስቴር ዓብይ አህመድ ጥሪያችንን እናቀርባለን።

በሀገራችን በቅርብ ጊዜ ለተፈጠረው ቀውስ ዋና ተጠያቂዎች፤ በህገ ወጥ መንገድ ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን አፈንግጠው የወጡት ሊቃነ ጳጳሳት እንደሆኑ ግልጽ ነው፤ በጣም ያሳዘነንና ያስገረመን ግን፤ የበርካታ ንጹሀን ምእመናን ህይወት በኦሮሚያ ክልል የጸጥታ ሰወች በከንቱ ሲቀጠፍ፤ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያንም ክብሯ ሲገፈፍና ከባድ ዉድመት ሲደርስባት እያየ፤ የኢትዮጵያ ፌደራል መንግሥት ህግን የማስከበርና የዜጎችን ደህንነት የመጠበቅ ኃላፊነቱን በሚገባ አለመወጣቱ ነው።

በሚልዮን የሚቆጠር የኢትዮጵያ ሕዝብ ዳያስፖራዉን ጨምሮ፤ በመንግሥት ላይ ያለው እምነቱ በፍጥነት እየተሸረሸረ ለመሄዱና፤ ቀውሱንም ለመፍታት ያለው ፍላጎት አነስተኛ መሆኑ ብቻ ሳይሆን፤ እራሱ አውቆ የፈጠረዉና የሚደግፈው ነው እያለ ማመን እንደቀጠለ በግልጽ የሚታይ ነው።

በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን፤ አሜሪካንን ጨምሮ በመላዉ ዓለም ዙሪያ የሚኖሩ ኢትዮጵያዉያን፤ በሀገራቸው ላይ እየተሠራ ያለዉን ከፍተኛ ግፍና የንጹሀን ዜጎች ህይወት በከንቱ መቀጠፍ፤ ምን ያክል እንዳሳሰባቸዉና እንዳስጨነቃቸው በቁጭት ብቻ ሳይሆን በጸሎትና በሰላማዊ ሰልፍ እየገለጹ ይገኛሉ።

በሌላ ወገን፤ ተሰሚነት ያላቸውና በሕዝቡ ዘንድ የተከበሩ ታላላቅ ኢትዮጵያዉያን፤ በቤተክሲያኗና በመንግሥት መካከል ያለዉን ልዩነትና አለመተማመን በማጥበብ፤ ሁለቱን

አቀራርቦ በሽምግልና ሰላም ለማዉረድ የጀመሩትን ጥረት ከልብ እንደግፋለን፤ እንዲሳካላቸዉም ምኞታችን ነው።

ይህን አስመልክቶ፤ የኢትዮጵያ ሀይማኖቶች ካዉንስል፤ ለኢትዮጵያ መንግሥትና የተለያዩ ፖለቲካ ፓርቲወች፤ ለብዙሀን መገናኛ አካላትም ያስተላለፈዉን መልእክት፤ ተቋማቱ በተቻለ መጠን ኃላፊነት የሞላበትና ህጋዊ መንገድን የተከተለ መፍትሄ ለመሻት፤ የበኩላቸዉን አስተዋጽኦ እንዲያደርጉና፤ ካዉንስሉን በመደገፍ፤ ቤተክርስቲያኗ ያለምንም የዉጭ ጣልቃ ገብነት የዉስጥ ችግሯን በራሷ ህግና ሥርአት ለመፍታት አቅም እንዳላት እንዲገነዘቡ ያሳሰበዉን ሙሉ በሙሉ እንደግፋለን።

ይሁን እንጅ በአንጻሩ እንደሚሰማዉ፤ በኦሮሚያ ክልል የጸጥታ አካላት በቢተክርስቲያኗ ላይ እየደረሰ ያለዉን በደልና ግፍ፤ በቅዱስ ሲኖዶሱ የተመደቡ የሀይማኖት መሪወችን እንግልትና እስር፤ ወደሀገረ ስብከታቸው እንዳይገቡ መከልከል፤ ከዚያም አልፎ ምእመናንን በጭካኔ መግደል፤ ያፈነገጡትንና በቅዱስ ሲኖዶሱ የተወገዙትን ሊቃነ ጳጳሳት በመደገፍ፤ ህግ በመጣስ የአብያተ ክርስቲያናትን በር እየሰበሩ እንዲገቡና ክብሯን እንዲደፈሩ፤ ሀብትና ንብረቷን እንዲወርሱ መንግሥት ማደፋፈሩን በጥብቅ እንቃወማለን።

በጥር 27 ቀን 2015 ዓም (February 4, 2023) እንደሚባለው፤ በሻሸመኔ ከተማ ከ30 በላይ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ምእመናን፤ በኦሮሚያ ክልል የጸጥታ አባላት በግፍ መገደል ኤፓክን ከልብ አሳዝኖታል፤ ይህ አሰቃቂና አስደንጋጭ በንጹሀን ዜጎች ላይ የደረሰ ግፍ ተጣርቶ፤ ወንጀሉን የፈጸሙት ለፍርድ እንዲቀርቡ በጥብቅ እናሳስባለን።

ጠቅላይ ሚንስቴር ዓብይ አህመድና መንግሥታቸው፤ ለህገመንግሥቱና ለሀገሪቱ ህግ የበላይ ጠባቂ መሆናቸውን በመገንዘብ፤ ኃላፊነት ተሰምቷቸው፤ አቅጣጫቸዉን እንዲያስተካክሉና፤ ሀገራችንን ከከፋ መቅሰፍት እንዲያድኑ፤ የጥንታዊቷን የሀገር ቅርስና ባለዉለታ የሆነችዉን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያንና፤ የምእመናኖቿን ህጋዊ ጥያቄና፤ የኢትዮጵያን ሕዝብ ጩኸት በማዳመጥ ችግሩን በሰከነ ሁኔታ በብስለት፤ በብልሀትና በሰላማዊ መንገድ እንዲፈቱ በአጽንኦት እናሳስባለን።

ችግሩ በቶሎ ካልተፈታና እየተባባሰ ከሄደ፤ ሀገራችን በፊት በታሪኳ ካጋጠሟት ሁሉ ከፍተኛ ቀውሶች የባሰና መዉጫ የማይገኝለት አዙሪት ዉስጥ እንዳትገባ ያሰጋል፤ ጠ/ሚኒስቴሩንም ቢያንስ በታሪክ ተወቃሽ ሊያደርጋቸው ይችላል፤ ይህን የእኛንና በሚልዮን የሚቆጠሩ ኢትዮጵያዉያንን ጩኸት አዳምጠው፤ መፍትሄውን በቶሎ እንዲፈልጉና፤ ሀገራችንን በድንገት ከገባችበት ቀውስ ለማዳን ትክክለኛና ቆራጥ አመራር እንዲሰጡ ከልብ እንመኛለን፤ እንደሚሳካልዎትም ተስፋ አለን፤ የእርስዎ ስኬት የሀራችን የኢትዮጵያ ስኬት ይሆናልና!

P.O Box 636 Kennett Square PA 19348 • info@aepact.org • www.aepact.org

ፈጣሪ ኢትዮጵያንና ሕዝቦቿን ይጠብቅ!

መስፍን ተገኑ፤
የኤፓክ ፕሬዘዳንት
የካቲት 1ቀን 2015 ዓም
(February 8, 2023)